# ማስታወቅያ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪሰ ዩንቨርሲቲ ከኢፌድሪ ጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በመተባባር የጉምሩክ አስተላላፊነት የሙያ ፈቃድ ለማውጣት የሚያስፍልገውን ስልጠና ለመስጠት በዝግጅት ላይ ይገኛል። በመሆኑም ስልጠናውን ለመውሰድ የመግቢያ ፈተና የሚሰጥ በመሆኑ ፍላጎቱ ያላቸውንና የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ ሰዎችን መልምሎ ለማሰልጠን አቅዷል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩ መስፈርቶችን የምታሟሉ ሁሉ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ቀርባችሁ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**መስፈርቶች**

- ✓ በትምህርት ሚኒስቴር እውቅና ከተሰጠው ኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው/ያላት፣
- ✓ መሰረታዊ የኮምፒውተር አጠቃቀም እውቀት ያለው/ያላት፣
- ✓ ስልጠናው የሚወስደው ጊዜ ቅዳሜን ጨምሮ 36 ቀናት ሲሆን ለስልጠናው የሚያስፈልገውን የአገልግሎት ክፍያ /ወጪ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነ/የሆነች

**የምዝገባ ሁኔታ**

- ✓ **የመመዝገቢያ፡-** CMC መንገድ በሚገኘው የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ- አባይ አዳራሽ
- ✓ **የምዝገባ ቀን፡-** ከሰኔ 18 ቀን እስከ ሰኔ 23/2011 ዓ.ም. በስራ ሰዓት እና እሁድ እስከ 6 ሰዓት ድረስ
- ✓ **የመመዝገቢያና የፈተና ክፍያ፡-** በያንዳንዱ ሰው 1ሺ300 ብር
- ✓ **የመግቢያ ፈተና የሚሰጥበት ቀን፡-** ለእያንዳንዱ ተመዝጋቢ የመፈተኛ ቁጥርና የመፈተኛ ቦታ ቀንና ሰዓት በዩኒቨርስቲው ድረ ገፅ እና በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡

ስለዚህ በስልጠናው መሳተፍ የምትፈልጉ ዜጎች በተጠቀሰው ጊዜ የዶክመንታችሁን ዋናውን እና ኮፒ ይዛችሁ ከዚህ ጋር የተያያዘው **የመመዝገቢያ ፎርም** በትክክል በመሙላት በአካል ቀርባችሁ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

# ዩኒቨርስቲው